# ቦንቡን ትተው፤ ቦንድ ስለገዙት ወገኖች...

ሰለሞን ሽፈራው 08-24-17

የዛሬዋ ኢትዮጵያ ዓይነተኛ መገለጫዎች ተደርገው የሚወሰዱ ጉልህ ነባራዊ እውነታዎች አሉ። ኢትዮጵያ አሁን ላይ የምትገኝበትን ተጨባጭ እውነታ ከሚያሳዩ የበጎ ገፅታዎቻችን አይነተኛ መገለጫዎች መካከል፤ በተለይም ሀገራችን የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ጭምር ቀልብ እየሳበ እንደመጣ በሚታመንበት የዕድገትና ብልፅግና ግስጋሴ ላይ የመኖሯ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ የተነሳም የዛሬዋ ኢትዮጵያ በፈጣን የልማት ጉዞ ላይ ከሚገኙ ጥቂት የዓለማችን ታዳጊ ሀገራት መካከል አንዷ ስለመሆኗ ዓለም ዓቀፋዊ የምጣኔ ሀብት ጥናትና ምርምሮች ጭምር ያመክታሉ።

ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቆመውን የሀገራችን በጎ ገፅታ የሚያደብዘዝ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ረገድ ቀላል የማይባል ፈተና እየጋረጡብን ያሉ ተግዳሮቶችም መኖራቸው የሚካድ ጉዳይ አይደለም። በተለይም ደግሞ ካለፈው ዘመን የፖለቲካዊ ታሪካችን ጋር ተያይዞ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ክፉ ባህል ተደርጎ ሊወሰድ በሚችል መልኩ የሚገለፁ ሀገራዊ ችግሮች አሁንም ድረስ ክፉኛ ሲፈታተኑን የሚስተዋሉበት አግባብ እንዳለ ስንገነዘብ የጉዳዩ ውስብስብነት ያሳስበን ዘንድ ግድ ነው ማለት ይቻላል። እናም እኔ ከዚህ አኳያ ላነሳው የፈለግኩት ነጥብ ቢኖር፤ ሀገራችን የምትመራበትን ፌደራላዊ ስርዓት በሃይል ለማስወገድ ያለመ የትጥቅ ትግል እንደሚያካሒዱ የሚነገርላቸው ሽብርተኛ ቡድኖች በአስመራው አገዛዝ ጉያ ውስጥ ተወሽቀው የአቶ ኢሳያስን ፀረ ኢትዮጵያ ስትራቴጂ ለማስፈፀም ሲሞክሩ የሚስተዋሉበትን አፍራሽ እንቅስቃሴ የሚመለከት ስለሆነ አሁን በቀጥታ ወደ ዋነኛው የፅሁፌ ማጠንጠኛ ርዕሰ ጉዳይ አልፋለሁ።

እንግዲያውስ፤ የጎረቤት ኤርትራ ነውጠኛ አገዛዝ ከትናንት እስከዛሬ በውል የሚታወቅበትን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር እንዳትቀጥል ለማድረግ ያለመ የትርምስ ስትራቴጂ እንዲያስፈፅሙለት፤ ከእያንዳንዱ የብሔር-ብሔረሰብ ህዝብ መካከል አኩራፊ ፖለቲከኞችን አፈላልጎ በመደለልና በማስደለል ወደ አስመራ ካስኮበለለ በሁዋላ አሰልጥኖና አስታጥቆ ለጥፋት ተልዕኮ የሚያሰማራበትን የመንግስታዊ ሽብርተኝነት ተግባር ስላጋለጡ ወገኖች ጉዳይ ነው እንድናወጋ የፈለግኩት። ስለዚህም የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ግፈኛ አገዛዝ <<የሙሉ ጊዜ ስራ>> አድርጎ እንደወሰደው የሚነገርለትን፤ ኢትዮጵያን በብሔር ብሔረሰብ ህዝቦቿ የዕርስ በርስ ፍጥጫና መናቆር ምክንያት ለብተና አደጋ እንድትጋለጥ የማድረግ ዕኩይ ዓላማ ለማሳካት ሲል የሚያውጠነጥነውን እቺን ሀገር የማተራመስ ሴራ ወደ ተግባር የመለወጥ ዓላማ አስይዞ ከሚያዘምትብን የሽብር ቡድኖች መካከል፤ ስህተታቸውን የሁዋላ ሁዋላ የተገነዘቡ ዘጠና ሁለት ግለሰቦች በቅርቡ የሚያስገርም ውሳኔ ላይ ደርሰዋልና እርሱን አንስተን ጥቂት እንጨዋወት።

ማለትም፤ በሻዕቢያ አገዛዝ ጉያ ውስጥ ተወሽቀው የዛሬዋን ፌደራላዊት፤ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ለማተራመስ ያለመ የሽብርተኝነት ተግባር የመፈፀም ተልዕኮ እየተቀበሉ በመንቀሳቀስ ከሚታወቁት ቡድኖች መካከል አንዱ እንደሆነ የሚነገርለትን <<የቤንሻጉል ጉምዝ ህዝቦች ነፃ አውጭ ግንባር >> የተሰኘ ቡድን ይመሩት የነበሩ ግለሰቦችን ጨምሮ፤ በቁጥር 92 የሚደርሱ የቡድኑ አባላት ናቸው ከጥቂት ሳምንታት በፊት ወደ ሱዳን ገብተው ካርቱም ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እጃቸውን የሰጡት። በርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ላለፉት ጥቂት ዓመታት ተደጋግሞ ሲደረግ የተስተዋለ ጉዳይ እንጂ ዛሬ ላይ ብቻ የተከሰተ አዲስ ነገር አይደለም ማለት ይቻላል። ለዚህም ደግሞ በ2007ዓ/ም መጨረሻ ላይ የአቶ ሞላ አስገዶም ቡድን ከነሙሉ ትጥቁ ከኤርትራ ቀጥታ ወደ

ኢትዮጵያ የተመለሰበትንና እንዲሁም በ2009ዓ/ም << የአፋር ህዝብ ነፃ አውጭ ግንባር>> ከተሰኘ ቡድን አባላት መካከል የተወሰኑት የወሰዱትን ተመሳሳይ እርምጃ እንደምሳሌ ማስታወስ ተገቢነት ይኖረዋል።

ይሁን እንጂ ግን፤ የዘንድሮዎቹ ተረኞች ሰሞኑን ከወደ አሶሳ በተደመጠ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዜና ላይ ሲናገሩ የሰማሁትን ያህል ትርጉም የሰጠኝ ጠቃሚ መልዕክት የለም ማለት እችላለሁ። ምክንያቱም ደግሞ በአንድ ዶክተር የሚመሩትና ራሱን <<የቤንሻጉል ጉምዝ ህዝቦች ነፃ አውጭ ግንባር>> እያለ የሚጠራውን የሽብር ቡድን ከድተው በመምጣት ለክልሉ መንግስት እጃቸውን የሰጡት 92 ግለሰቦች፤ ሐሙስ ነሀሴ 4 ቀን 2009ዓ/ም አየር ላይ ለዋለው የኢ.ቢ.ሲ. ዜና እንደሰጡት ማብራሪያ ከሆነ፤ በእርግጥም ውሳኔያቸውን አንስተን ለአርአያነት እናወሳው ዘንድ የሚጋብዝ ጠቃሚ ጎን ያለው ሆኖ ይሰማኛልና ነው።

ለአብነት ያህልም የቡድኑ መሪ ስለመሆናቸው የተነገረላቸውን ዶክተር ስለወሰዱት የተሃድሶ ስልጠና ጠቀሜታና እንዲሁም ደግሞ ወደ ፊት በክልሉ የልማት ሂደት ስለሚኖራቸው አወንታዊ ሚና ያብራሩለት ዘንድ የዜናው ዘጋቢ ጋዜጠኛ ጠይቋቸው ሲመልሱ << እንግዲህ በቅድሚያ ልገልፅልህ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር እኛ በኤርትራ መንግስት ድጋፍና ትብብር ስር እናካሒድ የነበረውን የትጥቅ ትግል ትተን ለመምጣት የተገደድንበት ዋነኛ ምክንያት፤ የኢትዮጵያን የህዳሴ ሃይል ማመንጫ ግድብ የግንባታ ሂደት ለማስቆም ያለመ የሽብር ጥቃት እንድንፈፅም በሻዕቢያ አመራር የተሰጠንን ግዳጅ ተቃውመን ነው። ምክንያቱም ደግሞ ይህ በኛው ክልላዊ መስተዳደር ውስጥ እየተገነባ ያለው የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ሀገራችን በመሰረታዊ የለውጥ ጉዞ ላይ እንደምትገኝ የሚያሳይ ፕሮጀክት እንደመሆኑ መጠን፤ እርሱን እንድናጠቃ የተሰጠንን ግዳጅ መቀበል ማለት ታሪክ ይቅር የማይለውን ስህተት እንደመፈፀም ሊቆጠር ይችላልና ነው>> የሚል አሳማኝ ሀሳብ መሰንዘራቸውን ሰምቻለሁ።

በእርሳቸው እየተመሩ ከኤርትራ ምድር ወደ ሀገራቸው ስለተመለሱት 92 የሽብር ቡድኑ የቀድሞ አባላት፤ ቀጣይ እቅድ ሲያስረዱም ዶክተሩ << ከዚህ በኋላማ እኛም የክልላችንና የሀገራችን ህዝቦች የልማት ጉዞ አካል ሆነን መቀጠል ነው እንጂ ሌላ ምን ዓላማ ይኖረናል ብለህ?>> በማለት ጠያቂውን ጋዜጠኛ መልሰው ጠይቀውታል። እርሳቸውን ጨምሮ ሁሉም የወዶ ገብ ቡድኑ አባላት በነፍስ ወከፍ የአስር ሺህ ብር ቦንድ በመግዛት፤ ለታላቁ የኢትጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የግንባታ ሂደት መፋጠን እንደ ዜጋ የሚጠበቅባቸውን አወንታዊ ድርሻ የመወጣት ጥረት እንደጀመሩም ነው የ.ኢ.ቢ.ሲው ዜና ላይ የተገለጸው።

ታዲያ ይህ ዓይነቱ ለጥፋት ተግባር ማስፈፀሚያ እንዲያውሉት ታስቦ በፀረ ኢትዮጵያ ሃይሎች አማካኝነት እንዲታጠቁ የተደረጉትን የግድብ ማውደሚያ ቦምብ ፈትተው በመጣል ለሀገር ልማት የሚጠቅም ቦንድ ለመግዛት የወሰኑበት የተቀደሰ የአቋም ለውጥ የአስመራውን ነውጠኛ አገዛዝ መንግስታዊ ሽብርተኝነት ደግፈው ለቆሙት ፅንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖችም ጭምር ትምህርት ሊሰጥ የሚችል አይደለምን? ደግሞስ ከቀደመ ስህተታቸው እየተማሩ፤ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደሉትን ሀገርና ወገን ለመካስ መዘጋጀታቸውን የመግለፅ ድፈረት የታደሉ ፖለቲከኞችን እንደማየት ምን መልካም ነገር ይኖራል ወገኖቼ? እንደኔ እንደኔ ከሆነ ግን ተጠቃሾቹ ወገኖች ቦምቡን ጥለው ቦንድ ሲገዙ የተስተዋሉበት ክስተት፤ በተለይም ለሀገራችን የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ እንደ መልካም ጅምር ሊወሰድ የሚችል ይመስለኛል።

ከዚሁ ቅን እምነቴ በሚመነጭ ተስፋ ለሌሎቹ የሻዕቢያ መንግስት ጉዳይ አስፈፃሚ ቡድኖች አባላትም ጭምር ይበጃል የምለውን የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት መልዕክት ላስተላልፍና ማስታወሻዬን አጠቃልላለሁ። ስለሆነም፤ የአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ማፍያ አመራር የኢትዮጵያን ዕድገት ከማይመኙ አገራት ከሚደጎመውና ከኤርትራ ህዝብ

ጉሮሮ ላይ እየቀማ በሚሰፍርላቸው ቀለብ አማካኝነት << የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ እያካሄድን ነው>> እያሉ የገዛ ራሳቸውን ጭምር ሲያታሉ የሚስተዋሉት የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፅንፈኛ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሁሉ፤እንደተለመደው በ<<ካፈርኩ አይመልሰኝ>> ዓይነት አጉል ድርቅናቸው ምክንያት ከሻዕቢያ ግፈኛ አገዛዝ ጋር ወደ ከርሰ መቃብር ለመውረድ ባይጠብቁ ይመረጣል የሚል ምክሬን እለግሳቸው ዘንድ ተገቢ መስሎ ይሰማኛል። አለበለዚያ ግን፤ ቦምቡን ትተው ቦንድ ለመግዛት የወሰኑትን የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል ተወላጆች መርተው የመጡት ዶክተር እንዳሉት ፤ ታሪክ ይቅር የማይለውን ድርብ ድርብርብ ስህተት በገዛ ራስ ሀገርና ወገን ላይ ከመፈፀም ያለፈ ውጤት ማምጣት እንደማይችሉ (የወቅቱን ዓለም አቀፋዊ እውነታ በማየት ብቻ) ከወዲሁ ደፍሮ መናገር ይቻላል። ወይም ደግሞ << የትጥቅ ትግል ዱሮ ቀረ!>> ብለን እንለፈው ጉዳዩን።

ለማንኛውም እኔ የዛሬውን ከማጠቃለሌ በፊት ቦንቡን ትተው ቦንድ ለመግዛት የወሰኑን ወገኖች ላድንቅ። ውሳኔያቸው ከቀደመ መሰል ስህተት የመማርና የጥፋት ተልኮ ማስፈጸሚያ ሆኖ ከመሞት ይልቅ ለራስ ሀገር ልማት ተሰልፎ የትውልድ ባለውለታ የሚያደርግ ሰናይ ተግባርን እየከወኑ ማለፍን የመምረጥ ፍቃደኝነት ላላቸው ወገኖች ሁሉ፤ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ ሆኖ እንዳገኘሁበትም ጭምር ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ። መቸስ <<ከሰው ስህተት፤ ከብረት ዝገት አይጠፋም>> አይደል የሚለው የሀገራችን ህብረተሰብ? ስለዚህ ከቀደመ ስህተታቸው ተምረው የምር በሆነ የመጸጸት ስሜት ወደ አእምራቸው መመለስን ለሚመርጡ ሀይሎች ሁሉ አድናቆቴ ልባዊ ነው። እናም ይህ ዓይነቱ ጠቀሚ ውሳኔ በሀገራችን የፖለቲካ ሀይሎች ዘንድ መለመድ ያለበት ገንቢ ባህል እንደመሆኑ መጠን፤ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩበት ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሂደታችን መፋጠን ይበጅ እንደሁ እንጂ ማንንም የሚጎዳ ጎን አይኖረውም የሚለው ቁልፍ ነጥብ ላይ አስመሬበት ሐተታዬን እዚህ ላይ ላብቃ። መዓ ሰላማት!!